የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 30th
ADDIS ABABA, 24th June, 2024

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፵፱

የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..................................................................................... ገጽ ፲፭ሺ፮፻፮

## ደንብ ቁጥር ፭፻፵፱/፪ሺ፲፮

## የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) (ሀ) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል ፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፵፱/ ፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሰረት ይተዳደራል፡፡

## Content

Regulation No 549

Ethiopian Conformity Assessment Enterprise Re-Establishment Council of Ministers Regulation ..................................................... Page 15606

## REGULATION NO 549/2024

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF ETHIOPIAN CONFORMITY ASSESSMENT ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Conformity Assessment Enterprise Re-Establishment Council of Ministers Regulation No 549 /2024."

2. **Establishment**

1/The Ethiopian Conformity Assessment Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby reestablished as a Federal Public Enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No.25 /1992.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 54.00 ብር

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

CamScanner

፮/ ከሀገር ውስጥ ወይም ከሌሎች የውጭ ሀገር የግል ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን እና የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን ለሽያጭ የማቅረብ፣ እና

፯/ አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን ፡፡

፮. <u>ካፒታል</u>

፩/ ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፬ ቢሊዮን ፯፻፸፮ ሚሊዮን ፬፻፵፬ሺ ፮፻፹፰ (አራት ቢሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር) ሲሆን ከዚህም ውስጥ ፩ ቢሊዮን ፩፻፺፬ ሚሊዮን ፩፻፲፩ሺ ፩፻፸፪ ብር ከ፳፪ ሳንቲም (አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አራት ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሃያ ሁለት ሳንቲም) በአይነትና በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

፪/ የተፈቀደው ካፒታል ጣሪያ እስኪደርስ ድረስ ድርጅቱ ከሚያስመዘግበው ዓመታዊ ትርፍ ላይ የመንግስት የትርፍ ድርሻ፣ ከሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ ድጋፍ እና ከመንግስት የሚገኝ የኢንቨስትመንት ድጋፍ በካፒታልነት እየተመዘገበ ለማስፋፊያነት እንዲውል ተፈቅዷል፡፡

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም ፡፡

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ፡፡

፱. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፮/፪ሺ፲ በዚህ ደንብ ተሽሯል ፡፡



6/ Provide for sale inputs and equipment's for laboratory testing services in conjunction with national or other foreign private institutions; and

7/ Carry out any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

6. <u>Capital</u>

1/ The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 4,776,444,688 (Four Billion Seven Hundred Seventy-Six Million Four Hundred Forty-Four Thousand Six Hundred Eighty-Eight Birr) of which Birr 1,194,111,172.22 (One Billion One Hundred Ninety-Four Million One Hundred Eleven Thousand One Hundred Seventy-Two Birr and Twenty-Two Cents) is paid up in cash and in kind.

2/ Until it reaches the authorized capital, the enterprise is allowed to use the government's profit share of its annual profit, donation and funds from government as a capital.

7. <u>Liability</u>

The Enterprise shall not be held liable beyond its total assets.

8. <u>Duration of the Enterprise</u>

The Enterprise is established for an indefinite period.

9. <u>Repealed Regulation</u>

The Ethiopian Conformity Assessment Enterprise establishment council of ministers regulation number 196/2010 is hereby repealed.

CamScanner

፲. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በደንብ ቁጥር ፩፻፺፮/፪ሺ፲ የተቋቋመው የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ተላልፈዋል።

፲፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

አብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

10. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>

All the rights and obligations of the Ethiopian Conformity Assessment Enterprise established under regulation number 196/2010 are hereby transferred to the Ethiopian Conformity Assessment Enterprise established pursuant to this Regulation.

11. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of June 2024

ABIY AHMED (DR.)

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

CamScanner